ወደ SY26-27 - DCPS ከትምህርት-በኋላ (Afterschool) የፕሮግራም-አሰጣጥ እንኳን-ደህና መጣችሁ!

በትምህርት ቤት ቀን መጨረሻ-ላይ፣ የDCPS ከትምህርት-በኋላ ጊዜ ፕሮግራሞች (Out of School Time (OSTP) - የከትምህርት-ቤት በኋላ ፕሮግራሞች፤ ተማሪዎችን በቀለም-ትምህርት እገዛ፣ በርካታ የማበልጸጊያ እንቅስቃሴዎችን፤ በDCPS አስተማሪዎች፣ ባለሙያተኛተኞች (paraprofessionals)፣ እና በአጋር-ድርጅቶች በሚሰጠው ላይ፤ ተማሪዎችን ያሣትፋል። ፕሮግራሙ እውን-ሊሆን የቻለው፤ በDCPS የገንዘብ-እርዳታ እና ከ'21st Century Community Learning Center' - በተሰጠ፣ እርዳታ/grant ነው። በትምህርት ዓመት 2026-2027፣ በ'ከትምህርት ቤት ሰዓት ውጪ ፕሮግራሞች (Out of School Time Programs (OSTP) ቁጥጥር የሚደረግለት፣ በ55 ትምህርት ቤቶች ውስጥ፤ ከትምህርት-በኋላ (Afterschool) ፕሮግራሞች ይሰጣሉ። **[በDCPS በእኛ ከትምህርት-በኋላ ድህረ-ገጽ/Afterschool website - አዲስና-ማሻሻያ የተደረገበትን የትምህርት-ቤት ዝርዝር/updated list - አለው]**: በOSTP ከትምህርት-በኋላ (Afterschool) ፕሮግራሞች ውስጥ የማይካፈሉ ትምህርት ቤቶች፣ ለተማሪዎች የራሳቸው የሆኑ ፕሮግራሞችን ሊሰጡ ይችሉ ይሆናል። ለተጨማሪ መረጃ፤ የተማሪያችሁን ትምህርት ቤት፣ እባካችሁ አነጋግሩ።

## ጠቃሚ-የሆነ መረጃ:

- የDCPS 'OSTP' ምዝገባ፤ በ'My Out of School Time DC (MOST-DC)' ፖርታል/portal ላይ - ለ2026-2027 የትምህርት-ዓመት፤ መገኘት-የሚችል ይሆናል። ከDCPS OSTP ምዝገባ የሚከናወንበት ጊዜ ከመከፈቱ-አስቀድሞ፤ ቤተሰቦች አካውንት እንዲፈጥሩ ወይም አዲስና-ማሻሻያ/update፣ የወላጅ መገለጫ/parent profileን እንዲያጠናቅቁ፣ እና ተማሪያቸው(ዎቻቸውን) እንዲያገናኙ/link-እንዲያደርጉ - ይበረታታሉ። **ከዚህ-በታች ያለውን አንብቡ፣ "ልጄን እንዴት ማስመዝገብ እችላለሁ?" አዲስ-ለሆኑ እና ተመልሰው-ለሚመጡ ቤተሰቦች/returning families የሚሆን - የማከናወኛ-ትዕዛዞች።**
- **የDCPS 'OSTP' ምዝገባ፣ ማክሰኞ፣ ሜይ (May) 19 ቀን 2026፤ በ10:00 AM - ይጀምራል። ወደ 'ከትምህርት-በኋላ (AFTERSCHOOL)' ለመመዝገብ፤ እዚህ ተጫኑ:** [most.dc.gov]
- የልጃችሁ ክፍል - በ'OSTP' አገልግሎት-የሚሰጠው መሆኑን [በዚህ ዝርዝር-ውስጥ ምልከታ-አድርጋችሁ ማረጋገጥ] ትችላላችሁ።
- የኦንላይን ምዝገባ ዘዴው፤ በሞባይል-ስልክ፣ በኮምፒውተር፣ ወይም በታብሌት/tablet ላይ - ይሠራል። እነዚህን ማናቸውንም ዲቫይሶች ማግኘት ካልቻሉ፣ በትምህርት ቤታችሁ ውስጥ፣ ኮምፒውተሮች የሚገኙ-ይሆናል። መቼ መጥተው መመዝገብ እንደሚችሉ ለማወቅ፣ እባክዎን ወደ ትምህርት ቤትዎ ይደውሉ። የዲሲ የሕዝብ መጽሐፍት-ቤቶችም፣ ለሕዝብ ጥቅም የሚውሉ ኮምፒውተሮች አሏቸው።
- OSTP፤ አስተማሪዎችን፣ ባለሙያተኞች (paraprofessionals)፣ እና የቦታው-መሪዎች (site leaders)ን፣ እየቀጠረ ነው። [መረጃዎችን-አግኙ እና እዚህ አመልክቱ።]

## የ'ከትምህርት-በኋላ (Afterschool) ፕሮግራሞች' ምን-ዓይነት አገልግሎትን ይሰጣል?

የ'ከትምህርት በኋላ (afterschool)' የጊዜ-ሰሌዳ፤ የአንድ-ሰዓት የቀለም-ትምህርት እርዳታን፣ ወደ 20 ደቂቃዎችን በግምት-ከሚወስድ - የቤት-ስራ መስሪያ ጊዜን አካትቶ ይሰጣል። እራት/Supper ወይም መክሰስ/snack፣ ለሁሉም ተማሪዎች ካለምንም ክፍያ፣ በነፃ ይቀርባል። ከ60-90 ደቂቃዎች-የሚሆን የማበልጸጊያ-እንቅስቃሴዎችም (enrichment

activities) ይሰጣሉ። የእንቅስቃሴ-ገጽታዎች የሆኑትን፤ እንደ ገጸ-ባህሪያት፣ ምስጋና-ማቅረብ፣ ጓደኝነት፣ ወይም ጸረ-ማንጓጠጥ (anti-bullying) ያሉትን-ሊያካትት የሚችል ሲሆን፤ እንዲሁም አካላዊ-እንቅስቃሴን፣ ስነ-ጥበባትን (arts)፣ ወይም STEM (Science, Technology, Engineering and Math)ን ሊያካትት-ይችላል። አንዳንድ-የማበልጸጊያ እንቅስቃሴዎች በDCPS ሠራተኞች የሚመራ፣ እና አንዳንዶቹ ደግሞ በአጋር-ድርጅቶች ይመራሉ። በማበልጸጊያነት የሚሰጡት እንቅስቃሴዎች፣ በየትምህርት-ዓመቱ ወቅት እና ከትምህርት-ቤት ወደ ትምህርት ቤት ሊለያይ-ይችላል።

ከፍተኛ-ጥራት ባለው ከትምህርት-በኋላ (afterschool) የፕሮግራም አሰጣጥ ውስጥ መካፈል፤ በትምህርት ገበታ ላይ መገኘትን፣ የቀለም ትምህርት ስኬትን፣ እና በመማር ላይ ባላቸው አመለካከት-ላይ ማሻሻልን እንዲሚያመጡ-እንዳደረገ ተረጋግጧል። ሁለት ከግማሽ ሰዓታትን በከትምህርት-በኋላ ፕሮግራሞች ውስጥ በየቀኑ የሚማሩ ተማሪዎች፣ ከሁለት ወራቶች ጋር እቻ ሆኖ የሚመጥን የመማሪያ ጊዜን ያገኛሉ።

## ከትምህርት-በኋላ (Afterschool) ፕሮግራሙ ሰዓታቶቹ፣ ምንድናቸው?

ከትምህርት-በኋላ (afterschool) ፕሮግራሙ፣ የትምህርት ቀኑ ካለቀ በኋላ የሚጀምር እና፣ በእያንዳንዱ የሙሉ-ቀን ትምህርት (በትምህርት ቤትዎ ሌላ ማስታወሻ እስካልተገለጸ ድረስ) በ6:00 pm የሚያልቅ ይሆናል።

## በየትኛው ክፍሎች ውስጥ ያሉ መካፈል ይችላሉ?

OSTP ፕሮግራሞች፣ ከPK3 እስከ 5ተኛ ክፍል ያሉ ተማሪዎችን - በመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ውስጥ፤ እና ከPK3 እስከ 8ተኛ ክፍል ድረስ - በትምህርት ካምፓሶች ውስጥ አገልግሎት ይሰጣል። በ'River Terrace'፣ ሁሉም የክፍል-ደረጃዎች ብቁ-የሆኑ ናቸው። ብዙ ትምህርት ቤቶችም - ከትምህርት ቤት ፕሮግራም ሰጪዎች ጋር - በክፍያ-ላይ መሠረት ያደረገ አገልግሎትን የሚሰጡ ወይም ነፃ ከትምህርት-በኋላ (afterschool) ፕሮግራሞች ከሆኑ እና ብዙ ቤተሰቦች የከትምህርት-በኋላ (afterschool) ቦታዎችን በማስፋፋት ለማገልገል-ከሚረዱ ጋር፤ የሚሰሩ-ናቸው። ስለሆነም፤ በየተለያየ ቦታዎች የሚገኙ እያንዳንዳቸው የ'OSTP' ፕሮግራም፤ የሚያገለግሉባቸው የክፍል-ደረጃዎች ሊለያዩ ይችላሉ። የትኛው አገልግሎት ሰጪ ለተማሪዎ የተለየ-የክፍል ደረጃ እንደሚያገለግል ለማወቅ፤ ትምህርት ቤታችሁን አነጋግሩ። በDCPS ከትምህርት-በኋላ ድህረ-ገጽ/Afterschool website ላይ በ55 ትምህርት ቤቶች ውስጥ የሚገኙ በደንብ-የሚታወቁ አገልግሎት-ሰጪዎችን ዘርዝረናል።

## ተማሪዬን እንዴት ማስመዝገብ እችላለሁ?

1. ለትምህርት-ዓመት 2026-2027፣ የልጅዎን የትምህርት ቤት ምዝገባ ሞልታችሁ አጠናቅቁ። **የትምህርት ቤት ምዝገባው-ተከናውኖ እስካልተጠናቀቀ-ድረስ፣ ወደ ከትምህርት-በኋላ (afterschool) የፕሮግራም-አሰጣጥ መመዝገብ-አይቻልም።** የትምህርት ቤት ምዝገባ፣ በአሁኑ-ጊዜ የተጀመረ እና፣ በትምህርት ቤታችሁ-ውስጥ፣ ወይም በhttps://enrolldcps.dc.gov/ ላይ መጠናቀቅ ይችላል።

2. በዚህ ድህረ-ገጽ ላይ ለመመዝገብ - የሞባይል-ስልክ፣ ታብሌት/tablet፣ ወይም ኮምፒውተርን - ተጠቀሙ:most.dc.gov

| አዲስ-ለሆኑ - ምዝገባዎች | ተመልሰው-የሚመጡ ተማሪዎች - ምዝገባዎች |
|---|---|
| በmost.dc.gov ላይ ጎብኙ፣ 'SIGN IN' የሚለውን-መምረጥ፣ እና "አሁን-መመዝገብ/Sign Up Now." | ወደ አካውንታችሁ most.dc.gov ግቡ/Log in አድርጉ። |
| ከአካውንታችሁ ስር የሚገኘውን - ወደታች-ከሚዘረዝረው/dropdown - የእናንተን፣ የወላጅ/አሳዳጊ | ከላይ-በቀኝ ማዕዘን በኩል፣ ወደታች-ከሚዘረዘረው-መምረጫ ውስጥ ለመምረጥ፣ የተማሪ መረጃ/Student Information ታብ/tabን - መክፈት። |

| | |
|---|---|
| መገለጫ (Parent/Guardian Profile)ን አስገብቶ-ማዘጋጀት። | |
| ከእናንተ የወላጅ/አሳዳጊ መገለጫ (parent/guardian profile) ስር፣ የተማሪ መረጃ/Student Information ታብ (tab)ን መምረጥ እና ተማሪያችሁን 'ማገናኘት/LINK' ማድረግ። | ለእያንዳንዱ ተማሪ፤ ለትምህርት ዓመት 2026-2027 አስፈላጊ-የሆነውን፣ የስምምነት-መስጫ ጥያቄዎችን ማጠናቀቅ። |
| የእናንተን የDCPS - ከትምህርት-በኋላ (Afterschool) ፕሮግራምን - በትምህርት ቤታችሁ ስም መፈለግ፣ እና ምዝገባው-በሚጀመርበት ጊዜ ላይ 'APPLY' የሚለው-ላይ መጫን። | አንድ-ጊዜ የእያንዳንዱ ተማሪ የስምምነት-መስጫው ከተስተካከለ/updated-ከሆነ በኋላ፣ ምዝገባው-በሚጀመርበት ጊዜ ማመልከት ትችላላችሁ! |
| **ምዝገባ የሚጀመረው፣ በሜይ (May) 19 ቀን 2026፣ በ10:00 AM ላይ ነው** | **ምዝገባ የሚጀመረው በሜይ (May) 19 ቀን 2026፣ በ10:00 AM ላይ ነው** |

3. የልጃችሁን ከትምህርት-በኋላ (afterschool) ምዝገባ በምታጠናቅቁበት ጊዜ፣ ልጃችሁ በፕሮግራሙ ውስጥ ተመዝግቦ-እንደሆነ፣ ወይም ደግሞ በተጠባባቂ-ዝርዝር ውስጥ መሆኑንና-አለመሆኑን የሚጠቁም የመጀመሪያ የኢሜል-ማረጋገጫ እና/ወይም የኤስኤምኤስ (SMS) መልዕክትን - ታገኛላችሁ። **ያሉት-ቦታዎች (Seats)፤ መጀመሪያ-ቀድሞ የመጣን፣ መጀመሪያ-አገልግሎት በመስጠት (first-come, first - served basis) የአሠራር-መንገድ፣ በታዎቹ ይሞላሉ።** ቦታ ከተገኘ፣ ልጃችሁ ከተጠባባቂ-ዝርዝር ውስጥ እንዲወጣ ያደርገዋል። ስለ ልጃችሁ ምዝገባ ያሉት ማንኛውንም አዲስና-ማሻሻያ ለውጦችን፣ በኢሜል ማረጋገጫ እና/ወይም የኤስኤምኤስ (SMS) መልዕክት - እንድታውቁት-ይደረጋል።

4. የ'ከትምህርት-በኋላ (afterschool)' ምዝገባቸው እስከሚረጋገጥ ድረስ፣ ማንም-ልጅ በፕሮግራሙ ውስጥ ገብተው-እንዲማሩ አይፈቀድላቸውም።

## በOSTP ከትምህርት-በኋላ (Afterschool) ውስጥ፣ ለመመዝገብ ችግር ከገጠመኝ፣ ምን ማድረግ አለብኝ?

ወደ እናንተ የ 'MOST' አካውንት ለመግባት/logging in ችግር-የገጠማችሁ ከሆነ፣ እባካችሁ - **በ'MOST' ድህረ-ገጽ ላይ - እርዳታ-መጠየቂያን፣** እባካችሁ አስገቡ።

የልጃችሁ ትምህርት ቤት በOSTP አገልግሎት-ማግኛ መሆንና-አለመሆኑን፣ ወይም-ደግሞ ልጃችሁ ለሚገኝበት-ክፍል ሌላ ፕሮግራም-ሰጪ እንዳለውና-እንደሌለው ለመመልከት፣ እባካችሁ 55 የትምህርት ቤቶች ዝርዝርን ተመልከቱ። ከዚያ ድርጅት ጋር በቀጥታ-ለመመዝገብ ሊያስፈልጋችሁ የሚችል እና ከ'OSTP' መመዝገብ አትችሉም። https://dcps.dc.gov/page/out-school-time-programs-ostp-sites.

አሁንም-ቢሆን ችግር ከገጠማችሁ፤ እባካችሁን - ትምህርት ቤታችሁን ሬጅስትራር/registrar ወይም 'OSTP'፣ በafterschool.dcps@k12.dc.gov ወይም በ(202) 442-5002 በመደወል - እርዳታ-ለማግኘት አነጋግሩ።

## ልጄ፣ በተጠባባቂ-ዝርዝር ውስጥ ነው/ናት። የሚቀጥለው እርምጃ ምንድነው?

የ'ከትምህርት-በኋላ (Afterschool)' ምዝገባው የሚከናወነው፤ መጀመሪያ-ቀድሞ የመጣን፣ መጀመሪያ-አገልግሎት በመስጠት (first - come- first - served basis) የአሠራር-መንገድ፣ በእያንዳንዱ-ትምህርት ቤት ውስጥ፣ በፕሮግራሙ ውስጥ ቦታዎችን-በመስጠት ይከናወናል። የትምህርት ቤቱ የ'ከትምህርት-በኋላ (afterschool)' ቦታዎቹ

በሙሉ ተይዘው ሲሞሉ፤ ተማሪዎች - እንደየተመዘገቡበት ቀንና ሰዓት ቅደም-ተከተል መሠረት፣ በተጠባባቂ-ዝርዝር ውስጥ ይገባሉ። በክፍል-ደረጃቸው ላይ አገልግሎት የሚሰጥ የ'ከትምህርት-በኋላ (afterschool)' ቡድን - ክፍት-ቦታ በሚገኝ-ጊዜ፤ ተማሪዎች ከተጠባባቂ-ዝርዝር ውስጥ ይወጣሉ። ለምሳሌ፤ በመዋዕለሕፃናት ቡድን ውስጥ፣ አዲስ የመዋዕለሕፃናት ተማሪን ለመጨመር የሚቻለው - በቡድኑ-ውስጥ ካሉት ተማሪዎች አንዱ በሚለቅ-ጊዜ ብቻ-ነው። 'OSTP'፤ በትምህርት-ገበታ ላይ መገኘት (attendance)ን የሚቆጣጠር እና፣ ወዲያው ክፍት-ቦታ እንደተገኘ፣ አዲስ ተማሪዎችን ከተጠባባቂ-ዝርዝር እንዲገቡ ይጋብዛቸዋል። የተማሪያችሁ ቦታ ክፍት-በሚሆን ጊዜ - በኢሜል አማካኝነት እንዲያውቁት ይደረጋል፤ ሆኖም-ግን፣ ለክፍል-ደረጃቸው ምንም-ክፍት ቦታ ካልተገኘ፤ በትምህርት-ዓመቱ ሙሉ - ተማሪው በተጠባባቂ-ዝርዝር ውስጥ የመቆየት-ሁኔታም ሊኖር ይችላል። 'OSTP' እና የትምህርት ቤት መሪዎች፤ ተጨማሪ የ'ከትምህርት-በኋላ (afterschool)' ፕሮግራም እንዲኖር-በማድረግ - የ'ከትምህርት-በኋላ (afterschool)' ቦታዎችን ለማስፋፋት እና በተቻለ-መጠን ብዙ-ተማሪዎች ለማገልገል እንዲቻል የሚችሉትን ጥረት ሁሉ በማድረግ ይሣተፋሉ፤ ነገር-ግን፣ አንዳንድ-ጊዜ ሁሉንም-ተማሪዎች ለማገልገል ካለን-አቅም በላይ የሆነ ቦታዎችን-የማግኘት ጥያቄ ይኖራል። ይህ ችግር፣ በዲሲ (DC) ውስጥ እየተከሰተ ያለ- እና፣ በአሜሪካ ዙሪያ በሚገኙ የ'ከትምህርት-በኋላ (afterschool)' ፕሮግራሞችም እየገጠመ ያለ - አስቸጋሪና ፈታኝ-ነገር ነው።

## የሚከፈል-ክፍያ አለው?

የ'OSTP ፕሮግራም' ካለምንም-ክፍያ የሚሰጥ ነው። ምንም-ክፍያ የለውም። በአንዳንድ-ትምህርት ቤቶች ውስጥ፣ በሌላ የከትምህርት-በኋላ (afterschool) ሰጪዎች ለተማሪዎች አገልግሎት-የሚሰጡ - በተወሰኑ ክፍሎች ውስጥ፣ ክፍያ-ሊጠይቁ ይችሉ ይሆናል። በ55 የትምህርት ቤቶች ቦታዎች ውስጥ የሚገኙ፤ በደንብ-የታወቁ አገልግሎት-ሰጪዎችን ዘርዝረናል። ካለ-ምንም ክፍያ አገልግሎቶችን፣ ሁሉም የ'ከትምህርት-በኋላ (afterschool)' ፕሮግራም፣ ላይሰጥ ይችላል።

## እንዴት ነው ከትምህርት-በኋላ (Afterschool) ፕሮግራሙ የሚገመገመው?

የ'OSTP' ፕሮግራም፤ በከፊል የገንዘብ እርዳታውን የሚያገኘው፣ በ'21st Century Community Learning Center grant (21CCLC)'፣ ከስቴት የትምህርት የበላይ ተቆጣጣሪ ቢሮ (Office of the State Superintendent of Education (OSSE) ነው። የትምህርት ዓመት 2024-25 21CCLC ከትምህርት-በኋላ (Afterschool) የትምህርት ዓመቱ ማለቂያ የግምገማ ሪፖርት በOSSE እና DCPS የተቀረፁ የፕሮግራም ዓላማዎችን የያዙ እና በDCPS የ'OSTP ከትምህርት-በኋላ (afterschool)' ፕሮግራም የቅርብ-ጊዜ የመረጃ-ስብስብ (data) ይዞ በተገኘው - በ2024-2025 የትምህርት ዓመት ውስጥ፣ እነዚህ ዓላማዎች ግባቸውን መምታት/አለመምታቱ ላይ ግምገማን ያደርጋሉ። በተጨማሪም፣ አቀራረቡ (presentation)፣ ስለ'21CCLC' እርዳታ፣ የፕሮግራም ስነ-ሕዝብ አወቃቀሮች ላይ፣ ከውጪ ግምገማ አድራጊ የተገኙ ቁልፍ ነገሮች፣ ከትምህርት-በኋላ (Afterschool) ፕሮግራሙ ጥንካሬዎች፣ እና በSY25-26 ትኩረት በሚሰጣቸው ነገሮች ዙሪያ - ዋጋ-ያላቸውን መረጃዎችን ይዟል። **ቁልፍ-የሆኑት ግኝቶች ማጠቃለያ፤ ከዚህ-በታች በሚገኘው ማገናኛ/link አማካኝነት-ሊገኝ ይችላል።** ጥያቄዎች፤ ወደ afterschool.dcps@k12.dc.gov - ሊላኩ-ይችላሉ።

**ስለ 'ከትምህርት-በኋላ (afterschool)'፣ ለሚኖሯችሁ ሁሉም ጥያቄዎች፤ እባካችሁን - በሚከተለው አነጋግሩ:**

ከትምህርት ቤት ሰዓት ውጪ ፕሮግራሞች (Out of School Time Programs): (202) 442-5002 ወይም ኢሜል afterschool.dcps@k12.dc.gov.

### አባሪ(ዎች):

**ተያያዥነት-ያለው ይዘት:**

የዲሲ የሕዝብ መጽሐፍት ቤት ድህረ-ገጽ -- ሰዓታት እና ቦታዎች https://www.dclibrary.org/plan-visit

**[2024-25 DCPS 21CCLC Evaluation Findings.pdf]**